# ሳምንታዊ ዜና ዘገባ
## ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ
## ጥር 23 ቀን 2001 ዓ.ም.

- አምባገነን የአፍሪካ መሪዎች የሚገናኙበትና የሚዝናኑበት ስብሰባ ለሦስት ቀናት ይደረጋል፣
- አዲስአበባ በከፍተኛ ጥበቃ ተወጥራለች፣
- የወያኔዉ መሪ መለስ ዜናዊ ካላቸዉ ንብረት ላይ ጥቂቱን ለፓርቲያቸዉ እንዲያስረክቡ ለባለስልጣናቱ ትዕዛዛ ሰጠ፣
- ኦህዴዶች ተግባራዊ ማድረግ ጀመሩ፣<<ከተማ እያዉደለደልን ያገኘነዉ አይደለም>> በማለት ህወሀቶች ተቃዉሞ አሰሙ፣
- የሊቢያዉ መሪ ሙአመር ጋዳፊ ልጅ የነዳጅ ኩባንያ ኢትዮጵያ ዉስጥ ስራዉን ጀመረ የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል።

ዝርዝሩን ከሚቀጥለዉ ገፅ ጀምረዉ ያንብቡ <<>>

ለስሙ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ናቸው የተባሉት አምባገነኖች የሚሰባሰቡበት ስብሰባ ከጥር 23 ቀን እስከ ጥር 25 ቀን 2001 ዓ. ም. ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ ይደረጋል በሚል በፌዴራል ፖሊስ፤ በመከላከያ ሰራዊት፤ በአዲስ አበባ ፖሊስ እና በደህንነቶች ጭምር ተወጥራ እንደምትገኝ ታወቀ::

ህዝባቸውን እየረገጡ ከህዝቡ ፈቃድ ውጭ የስልጣን እድሜያቸውን እያራዘሙ የሚገኙት አምባገነን የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ለ3ቀናት በአዲስ አበባ ስብሰባ የሚያደርጉ ሲሆን ለስሙ አጀንዳ ተይዞ ያለ ቢሆንም ጥርስ የሌለው አንበሳ በመሆኑ ተፈፃሚነቱ እጅግ አጠራጣሪ እንደሚሆን የቀድሞው ልምድ አመላካች መሆኑ እየተነገረ እንደሚገኝ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

ከጥር 18 ቀን 2001 ዓ. ም. ጀምሮ የአፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ በዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ ሲካሄድ ቆይቶ ጥር 23 ቀን 2001 ዓ. ም. ደግሞ የመሪዎቹ ስብሰባ እንደተጀመረ የገለፀው የደረሰን ዘገባ መሪዎቹ ይገባሉ በተባለበት ከጥር 22 ቀን 2001 ዓ. ም. ጀምሮ አዲስ አበባ ከተማና ህዝቡዋ እጅግ ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ እንደሚገኙ ተዘዋውሮ የተመለከተው ዘጋቢያችን አረጋግጦዋል::

አምባገነን እና ህዝቦቻቸውን ረግጠው የራሳቸውን ፍላጎት ብቻ የሚያመቻቹት እነዚሁ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ከደሀ ህዝቦቻቸው አፍ ላይ በሚነጥቁት ገንዘብ በስብሰባ ስም አዲስ አበባ ከተማ ተንደላቀውና የ14 ዓመት ወጣት ህፃናትን ሲያማግጡ ሰንብተው ያለ አንዳች ውጤት የሚበተኑት እነዚሁ አምባገነን መሪዎች እንደ ጆፌ አሞራ እርስ በርስ ሲጨዋጨዋሁ ሰንብተው አንዱ የአንዱን ስህተት ሳይነግር ይልቁንም እየተሞካሻሹ የሚበተኑበት መሆኑንም ከእስከ ዛሬው ልምዳቸው ማረጋገጥ ተችሎዋል ሲል ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

የአፍሪካ ህብረት መስራችና ዋና መቀመጫ የሆነችው ኢትዮጵያ በአምባገነኑ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ህዝቡዋ እየተረገጠ እና እየተሰቃየ የእለት ጉርስ አጥቶ የእርዳታ ያለህ እያለ እየጮኸ ባለበት በዚህ ወቅት በስብሰባ ስም አዲስ አበባ ውስጥ ለቀናት የሚምነሸነሹት የአፍሪካ መሪዎች እያዩና እያስተዋሉ ሰምተው እንዳልሰሙ አይተው እንዳላዩ ሆነው ኮረዳ ሲያሞናሙኑ ሰንብተው የሚመለሱበት መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች አንዱ አንዱን ስህተት ማረምና መንገር የማይችሉ ወኔ የሌላቸው ሁሉም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው ሲሉ አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ሲገልፁ ተደምጠዋል::

የአፍሪካ ፀሐፊዎች ሆነው የሚመረጡትን እና የሚሾሙትን እነ መለስ የሚመቹዋቸውን ከማስመረጥ ጀምሮ እስከ ማስፀደቅ ድረስ በሀገሪቱ ሀብት እንዳሻቸው የሚፈነጩበት እና የሚጫወቱበት ሳይበቃቸው ቀድሞ ሳሌም አህመድ ሳሌም ቀጥሎም አልፋ ኮናሬን በጥቅምና በሴት እየደለሉ በህዝባቸው ላይ የሚያደርሱትን በደል እና ግፍ

እንዲሸፍኑላቸው ሲያደርጉ የቆዩት እነመለስ ዜናዊ አሁንም በዚያው መንገድ እየተጠቀሙ መሆኑን መምህሩ አስረድተዋል።

በ1997 ዓ.ም. በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ በተደረገ ሀገር አቀፍ ምርጫ ሙሉ ለሙሉ በዝረራ የተሸነፈው የወያኔን ቡድን «እንኳዋን ደስ አላችሁ በድል ተወጥቶዋል» በማለት ወያኔ እንዳሸነፈ በማስመሰል የገለፀው አልፋ ኮናሬ ከወያኔ ጋር ሆኖ ንፁህን ዜጎችን ያስጨፈጨፈ አምባገነን እና ለጥቅሙ የኖረ ግለሰብ መሆኑን የገለፁት እኚሁ ምሁር መቼም ቢሆን መቼ ወያኔና አልፋ ኮናሬ በኢትዮጵያ ላይ የሰሩት የግፍ ግፍ እንደማይረሳና ታሪክና ትውልድ ወደፊት ወቅቱን ጠብቀው ተጠያቂ እንደሚያደርጉዋቸው አይቀሬ መሆኑን ገልጸዋል።

አምባገነን መሪዎች የተሰባሰቡበት ስልጣናቸውን በህዝብ ድምጽ ሳይሆን በጦር መሳሪያ የሚይዙትና ብሎም የሚያስጠብቁት እነዚሁ ሰው በላ መሪዎች በየሀገሮቻቸው ህዝብ ሀብት እንደልባቸው እየተሸከረከሩ ህዝቦቻቸውን ከኑሮ ወለል በታች አድርገው እነሱ የሚምነሸነሹ ህሊናቸው በስልጣን ጥማት የናወዘ ግለሰቦች የተጠራቀሙበት ድርጅት ከዚህ ቀደም ያመጣው ለውጥ የለም ወደፊትም አንጠብቅም ሲሉ እኚሁ ምሁር በንዴትና በእልህ ሲገልፁ ተደምጠዋል።

በጋምቤላ የሰው ልጅ እንደ እንሰሳ በመትረየስ ታጭዶ በአንድ ጉድጉዋድ መቀበራቸውን የምዕራባውያን ለጋሽ ድርጅቶችና የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሙዋጋቾች በይፋ ሲያወግዙና ሲያጋልጡ ትንፍሽ ያላለው የአፍሪካ ህብረት፤ በቅርቡ በኦጋዴን ውስጥ ዜጎች በርሀብና በችጋር እንደቅጠል ሲረግፉ እያየና እያወቀ ዝም ብሎ አለም አቀፍ ሚዲያዎች ወደ ስፍራው ሲያመሩ ጉዴ ይጋለጥብኛል ብሎ አስከሬናቸውን ሰብስቦ እያቃጠለ መሆኑን በምስል አስደግፈው የተጋለጡት እነመለስ ዜናዊን መገሰፅ እና ብሎም መናገር ያልቻለው የአፍሪካ ህብረት አሁን ደግሞ የወያኔ ጦር በሱማሊያ ውስጥ ገብቶ በንፁህን ዜጎች ላይ ያደረሰውን ግፍና መከራ እያወቀ ምንም እንዳልተፈፀመ እያየ ያለ ድርጅት ለአፍሪካ ህዝቦች መከራንና ስቃይን እያራዘመ ለአምባገነኖች ከለላ እየሰጠ ያለ ድርጅት ከመሆን የዘለለ አይደለም ሲሉም መምህሩ ጨምረው ገልፀዋል።

በመላ አፍሪካ ውስጥ የሰው ልጆች እንደ ሳር በአምባገነን መሪዎች እየታጨዱ ባለበት እና ሁሉም አፍሪካዊ የመኖር ዋስትና ባጣበት በዚህ ወቅት እንኳዋን አንዱ መሪ የአንደኛውን ስህተት ከመናገር ይልቅ እርስ በርስ እየተሞከሻሹ እና እየተወዳደሱ በህዝቦቻቸው ላይ የሚያላግጡ መሪዎች የተሰባሰቡበት ድርጅት ስብሰባ ሰኞ ይጠናቀቃል ተብሎ ቢጠበቅም ከስብሰባው አንዳችም የሚጠበቅ ተስፋ እንደሌለ በርካታ የአውሮፓና የምዕራባውያን ዲፕሎማቶች እየገለፁ ናቸው።

ዛሬ የአፍሪካ ህዝብ መሰረታዊ ጥያቄ ዳቦ እና ዴሞክራሲ መሆኑ እየታወቀ ይህ ጥያቄ በአፍሪካ ሀገሮች ምላሽ ያገኘ ይመስል ባልረባውና ለህዝቡ አንዳችም ፋይዳ

በማይሰጠው አጀንዳ ላይ ሲዶልቱ ከርመው ትልቅ የህዝብ አጀንዳ ይዘው የከረሙ አስመስለው ቢቆዩም ትርጉም የሌለውና ለህዝቦች አንዳችም የማይጠቅም ፍፁም ራዕይ የሌለው በመሆኑ ከስብሰባው ምንም የሚጠበቅ ነገር እንደሌለም ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ለባለስልጣናቱ አዲስ መመሪያ አውጥቶ ትዕዛዝ ቢሰጥም ህወሀቶች ሊቀበሉት እንዳልቻሉ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ገለፀ፡፡

ባለፈው ሳምንት ውስጥ መለስ ዜናዊ ለአፍሪካ መሪዎች ምሳሌዎች ናቸው ለማሰኘት እና ለመወደስ ሲል ብሎም ሊያታልልበት የሚችለውን ሲያብላላ ከቆየ በሁዋላ ሰሞኑን ለባለስልጣናቱ መመሪያ አውጥቶ ትዕዛዝ ቢያስተላልፍም የህወሀት ባለስልጣናት በሙሉ የደማንበትና መስዋዕትነት የከፈልንበት በመሆኑ መመሪያውን አንቀበልም በማለት ትዕዛዙን ውድቅ ማድረጋቸውን የምንጮቹ ጥቆማ ገልፆዋል፡፡

ማንኛውም ከፍተኛ የኢህአዴግ ባለስልጣን እስካሁን ድረስ ካጠራቀመው ሀብት ውስጥ ጥቂቱን ለየፓርቲያቸው ገቢ እንዲያደርግ እና የጎደፈ ስማቸው እንዲታደስ እና በዓለም መሪዎች ዘንድ ስማቸውን ለማስጠራት ብሎ መለስ ትዕዛዝ ቢሰጥም የህወሀቶቹ እነ አርከበ እቁባይ ፤እነ አዜብ መስፍን፤ እነ ስዩም መስፍን እና ሌሎችም ከፍተኛ ባለስልጣናት የመለስን ትዕዛዝ ውድቅ አድርገው አቁዋም የወሰዱ ሲሆን፤ የብአዴኖቹ እነ አዲሱ ለገሰ ግን ምንም አቁዋም ሳይወስዱ መሀል ሰፋሪ ሆነው እንዳሉ የምንጮቹ ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

መለስን እንደ ጣኦት የሚመለከቱት ኦህዴዶች ግን ትዕዛዙ በተላለፈ በጥቂት ቀናት ውስጥ አባዱላ ገመዳ የኦህዴድ ምክር ቤትን ሰብስቦ የተሰጠውን መመሪያና ትዕዛዝ ተግባራዊ ማድረግ የጀመረ ሲሆን፤ አባዱላ ገመዳ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብቻ ሁለት ትላልቅ ህንፃዎች የሰራ ከመሆኑም በላይ በባንክ ብድር በቦሌ አካባቢ የመኖሪያ ቤት አሰርቶ አከራይቶት የነበረውን ቤት ለድርጅቱ ገቢ አድርጌያለሁ በማለት የተሰጠውን ትእዛዝ የፈፀመ መሆኑን የምንጮቹ ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

አባዱላ ገመዳ ከህዝብ በዘረፈው ሀብት ሁለት ህንፃዎች በአዲስ አበባ ውስጥ አሰርቶ እያከራየ መሆኑን የጠቆሙት የውስጥ አዋቂዎቹ ስለ እነሱ ምንም ትንፍሽ ሳይል በቅርቡ በቦሌ አካባቢ በባንክ ብድር የሰራውን ቤት ግን እስከ ተበደረበት ቡክ ለፓርቲዬ አስረክቤያለሁ ማለቱ አስገራሚ ነው ሲል የምንጮቹ ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

የኦህዴዱ ሊቀመንበር የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝደንት የተባለው አባዱላ ገመዳ ከመለስ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተግባራዊ ማድረግ የጀመረ ሲሆን ፤ሌሎቹም የእሱን አርአያነት እየተከተሉ እንዲፈፅሙ እያስገደደ መሆኑን የምንጮቹ

ጥቆማ ገልፆ የቀድሞው የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት ጁኔዲ ሳዶም አባዱላን ተከትሎ በናዝሬት ከተማ ውስጥ የነበረውን 500 ካሬ ባዶ መሬት ለፓርቲዬ አስረክቤያለሁ ሲል መግለፁን የምንጮቹ ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

ጁኔዲ ሳዶ አባዱላን ተከትሎ በናዝሬት የወሰደውን ባዶ መሬት አስረክቤያለሁ ይበል እንጂ በለገጣፎ አካባቢ ከህዝብ በዘረፈው ገንዘብ ከ5 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ አድርጎ ያሰራውን እጅግ ዘመናዊ መኖሪያ ቤቱን አስመልክቶ ምንም ትንፍሽ ሳይል መቅረቱንም የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ያስረዳል፡፡

የብአዴኖቹ እነ አዲሱ ለገሰ በባህር ዳር ፓፒረስ የተባለ ዘመናዊ ሆቴል እንዲሁም የደረቅና የፈሳሽ ማመላለሻ ከባድ መኪኖች እያሉዋቸው አንድም ታንፍሽ ሳይሉ እና ምንም አይነት አቋውም ሳይወስዱ እሺም የለ እምቢ እስከ ቅርብ ቀን ድረስ ዝምታን እንደመረጡ የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

፡

በህዝብ እና በሀገር ሀብት ላይ እነመለስ ዜናዊ የሰሩትን ያደፈና የቆሸሸ ታሪካቸውን ለመቀየር የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባን እንደ ጥሩ አጋጣሚ ተጠቅመው ስማቸውን ለማደስ እና ክብርና ዝናን ለመጎናፀፍ አስበው ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም እርስ በርስ ባለመስማማታቸው ሳይሳካላቸው እንደቀረም ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

የወያኔ ባለስልጣናት ከህዝቡ ላይ የዘረፉትን ሀብት ወደ ውጭ ከማሸሻቸውም በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ያሉትን ነባር ባለ ሀብቶች ተወዳዳሪ ሆነው ፋብሪካ እና ሌሎችንም ድርጅቶች አቋቁመው እየተንቀሳቀሱ እንደሚገኙም ታውቆዋል፡፡

የወያኔው ፕሬዝዳንት መቶ አለቃ ግርማ ወ/ ጊዮርጊስ ከአዲስ አበባ 14 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው አለም ገና ከተማ ቦታ በአቶ አባዱላ ገመዳ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ግንባታ የጀመረ ሲሆን ፤በተለይም ከ40 ዓመት እና ከዛም በላይ በአካባቢው ሲኖሩ የነበሩትን የአካባቢው ተወላጆች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እና የካሳ ክፍያ እንዲነሱ ለማድረግ በባለስልጣናቱ ጫና እየተደረገባቸው መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

መቶ አለቃ ግርማ ወ/ ጊዮርጊስ መሬት የወሰደ ከመሆኑም በተጨማሪ በቦታው ላይ ላሉት ነዋሪዎች ተለዋጭ ቦታ እና የካሳ ክፍያ ሳይፈጸምላቸው እንዲነሱ በማስገደዱ ህዝቡ ቁጣውን እየገለፀ እንደሚገኝም ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

ሁሉን ለራሴ ብቻ የሚሉት የወያኔ ባለስልጣናት ስልጣናቸውን መከታ በማድረግ በተለያዩ የንግድ ስራዎች ላይ እየተሰማሩ ነጋዴውን ህብረተሰብ ከጫወታ ውጭ ለማድረግ እየተንቀሳቀሱ ሲሆን በተለይ በፋብሪካ፤ በአስመጪ እና ላኪነት፤ በደረቅ እና ፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ዘርፍ፤ እንዲሁም በሌሎችም የንግድ ስራ ዘርፎች

ላይ ትኩረት አድርገው በሚስቶቻቸውና በዘመዶቻቸው ስም እየሰሩ መሆኑን ለማወቅ ተችሎዋል።

የህወሀቶቹ  አዜብ መስፍን በኮንስትራክሽን ስራ ላይ ፣ ስዩም መስፍን በሴራሚክስ ፋብሪካ ስራ ላይ ፣አርከበ እቁባይ ህንጻ በማከራየት ፣የብአዴኖቹ እነ አዲሱ ለገሰ በሆቲል ስራ ላይ ፣ በረከት ስምኦን በደረቅና በፈሳሽ ማመላለሻ ስራ ላይ ፣ተፈራ ዋልዋ በቆሻሻ ማስወገጃ ስራ ላይ ፣ ኦህዴዶቹ እነ ወርቅነህ ገበየሁ በአስመጪነት እና ላኪነት ስራ ላይ ፣እነ አባዱላ ገመዳ በአበባ እርሻ ስራ ላይ ፣ እነ ግርማ ብሩ በተለያዩ የንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው የሀገሪቱን ሀብት ከመበዝበዛቸውም በላይ የንግዱን ህብረተሰብ ለማሽመድመድ እየተሩዋሩዋጡ እንደሚገኙም ዘገባው አብራርቶዋል።

የወያኔ ባለስልጣናት በሚስቶቻቸው እና በዘመዶቻቸው ስም እየመዘበሩ ከሚያስነግዱት በተጨማሪ በውጭ ሀገር በተለይም በዱባይ ባሉ ባንኮች ውስጥ ከፍተኛ ገንዘብ እያሸሹ እና እያከማቹ ሲሆን ነጋዴውን ግን የውጭ ምንዛሪ አምጣ እያሉ የቁም ስቅሉን እያሳዩት መሆኑን  ዘገባው ጨምሮ ገልጾዋል።

መለስ ዜናዊ ሰሞኑን በውስጥ እና በውጭ ተከታታይ የሆነ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ኪሳራ እያጋጠመው ሲሆን በተለይ ከህወሀት ባለስልጣናት አሻፈረኝ ማለት በሁዋላም በቡና ላኪ ነጋዴዎች ዘንድም ከፍተኛ ቁጣና ተቃውሞ እንደገጠመው የደረሰን ዘገባ ገለፀ።

መለስ ዜናዊ እንደ ሁልጊዜው ሁሉ የቡና ላኪ ነጋዴዎችን ሰብስቦ አነጋግሮና አሳምኖ ሊሸኛቸው አስቦ የነበረ ቢሆንም ያሰበው ሳይሳካለት በሽንፈት እና በውርደት ተጠናቅቆ ሹልክ ብሎ ለመውጣት እንደተገደደ የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል።

በሀገሪቱ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ምንም አይነት የውጭ ምንዛሪ ገንዘብ ባለመኖሩ እቃዎች  እንደልብ ባለመግባታቸው ዋጋቸው  እየጨመረ ከፍተኛ የዋጋ መናር እያስከተለ ሲሆን በአንፃሩ ቡና ወደ ውጭ መላኪያ የውጭ ገንዘብ በመጥፋቱ በየመጋዘኑ ተከማችቶ እንደሚገኝ በንዴትና በእልህ ነጋዴዎቹ ለመለስ እንደገለፁለት ዘገባው አስረድቶዋል።

መለስ እስከ ዛሬ ድረስ እንደሚያደርገው ሁሉ በመቆጣት እንዲያም ሲል የማይሆነውን ሁሉ ይፈፀምላችሁዋል እያለ የውሸት ቃል እየገባ ለማሳመን ቢሞክርም በኪሳራ ውስጥ ያሉት የቡና ላኪ ነጋዴዎች እስከ ዛሬ ድረስ የተገባላቸው ቃል ምንም ያልተፈፀመላቸው ከመሆኑም በላይ ባዶ ተስፋ እንደሰለቻቸው በግልጽ ነግረውት አሁንም ከነሱ ምንም እንደማይጠብቁ መግለጻቸውን ዘገባው ገልፆዋል።

የቡና ላኪዎችን ሰብስቦ አሳዝኖና  አንጀት በልቶ  የውጭ ምንዛሪ  በብድር መልክ እንዲሰጡት  ነጋዴዎቹን የጠየቀ ቢሆንም ነጋዴዎቹ ግን መጀመሪያውኑ ከባንክ ጋር

በተሳሰረ መንገድ ቀጥታ ገቢ የምናደርገው ለባንክ መሆኑ እየታወቀ ይህ ጥያቄ እንዴት ሊነሳ ቻለ ሌላው ቢቀር በዓለም ላይ ከፍተኛ ተቀባይነት ያለውን ቡናችንን ልናጉዋጉዝበት የምንችልበትን የውጭ ምንዛሪ በማጣታችን ዛሬ በየመጋዘኑ ቡና ተከማችቶ ሊበሰብስ የተቃረበ መሆኑን እያወቃችሁ ምን እርምጃ ወስዳችሁዋል የሚሉና ሌሎችንም ጥያቄዎች በማንሳት በጥያቄ ሲያጣድፉት ወደፊት አብረን ተመካክረን እንሰራለን እናንተም ጋ ጥፋት አለ እኛም ጋ ጥፋት አለ ስለዚህ ይህ እዚሁ ላይ ይቁዋጭ ለወደፊቱ እያስተካከልን እንጉዋዛለን በማለት የተለሳለሰ ምላሽ ሰጥቶ እንደወጣም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ችግር ሆኖ ከተከሰተውና እነመለስን ናላ ከሚያዞረው አንዱ የነዳጅ እጥረት ሲሆን ፤ነዳጅ እንደልብ ከአለመኖር ጋር ተያይዞ የሸቀጦች እና የአህል ዋጋ በሚያስደነግጥ ሁኔታ እያሻቀበ መሆኑ ታወቀ::

በቅርብ ጊዜ የአንድ ኪሎ ስኩዋር ዋጋ 9 ብር ከ50 ሳንቲም የነበረው ዛሬ የአምስት ብር ጭማሪ አሳይቶ 14 ብር ከ50 ሳንቲም እየተሸጠ መሆኑንና የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋም ወደ 1300 ብር እያደገ መሆኑ ታውቆዋል::ነዳጅ በዓለም ገበያ ላይ ቀንሶ ያለበት ወቅት ቢሆንም ወያኔ ካዝና ውስጥ ምንም ምንዛሪ ስለሌለ እንደልብ ማስገባት ያልቻለ በመሆኑ የነዳጅ እጥረት በሀገር ውስጥ ሊከሰት እንደቻለም እየተነገረ ይገኛል::

ወያኔ የነዳጅ እጥረቱን በቀላሉ ለመቅረፍ በሚል ሰንካላ ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት ትላልቅ የምዕራባውያን ንብረት የሆኑት የነዳጅ ኩባንያዎችን እያስወጣ አዳዲስ አፍሪካ በቀል ኩባንያዎችን እየተካ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በቅርቡ የመጡት እና ስራ የጀመሩት የሊቢያ፤ የኬንያ እና የሱዳን ኩባንያዎች እንደሚገኙበትም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

የሊቢያው መሪ ሙአመር ጋዳፊ ልጅ ሀብት እንደሆነ የተነገረለት ኦይል ሊቢያ የተባለ ኩባንያ ሼል ኢዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ገዝቶ ስራ የጀመረ ሲሆን ሞቢል የነበረውን ደግሞ ኮቢል የተባለ የኬንያ ኩባንያ እና ናይል የተባለ የሱዳን ኩባንያ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ስራቸውን መጀመራቸው ታውቆዋል::

ኦይል ሊቢያ የእንግሊዝ ኩባንያ የነበረውን ሼል ሙሉ ለሙሉ ገዝቶ ስራ የጀመረ ሲሆን እስከ ዛሬ ድረስ ሼል ሲጠቀምባቸው የነበሩትን የ50 እና የ100 ብር ኩፖኖች ውድቅ አድርጎ ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ፍፁም በማይጣጣም መልኩ የ500 ብር ኩፖኖች ብቻ አሳትሞ ስራ ላይ በማዋሉ በርካታ መንግስታዊና የግል ድርጅቶች ለችግር መዳረጋቸውንም የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

የሶስት ኢትዮጵያውያን ንብረት እንደሆነ የሚነገርለት የተባበሩት ኩባንያ ብቻ ሀገር በቀል ሲሆን በአሁን ሰዓት ያሉት የነዳጅ ኩባንያዎች ከኢትዮጵያ ጋር በቀጥታም

ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ችግር ያለባቸው ሀገሮች የሊቢያ፤ የሱዳንና የኬንያ ድርጅቶች መሆናቸው ወደፊት ችግር ሊያስከትሉና ሀገሪቱንና ህዝቡዋን ለከፋ ስቃይ ሊዳርጉ ይችላሉ ሲሉ በርካታ ምሁራኖች ስጋታቸውን ከወዲሁ እየገለፁ ይገኛሉ፡